

# አስቴር

* አስቴር በምርኮ ከኢየሩሳሌም ከተወሰዱት እስራኤላውያን መካከል አንደኛዋ ናት። ወላጆቿ ከሞቱ በኋላም አጎቷ መርዶክዮስ ልክ እንደልጁ አድርጎ አሳደጋት።

* በዚያን ወቅት ንጉስ አርጤክስስ ንግስት የምትሆን ሴት ይፈልግ ነበር። በጣም ብዙ ልጃገረዶች ለዚሁ ታስበው ነበር። ነገር ግን ከአንድ አመት የውበት እንክብካቤ በኋላ አስቴር ንግስት እንድትሆን ተመረጠች።

* በንጉስ አርጤክስስ ግዛት ውስጥ ሃማ ኃያል ባለስልጣን ነበር። አይሁዳውያንን ለመግደል ያሴረ ክፉ ሰው ነበር።

* መርዶክዮስ ንጉሱ ዘንድ ገብታ ስለ አይሁዳውያን ሕይወት ትለምነው ዘንድ መልእክት ላከባት። ሳትጠራ ወደንጉሱ ዘንድ መግባት ሕይወቷን እንድታጣ ሊያደርጋት ይችላል። ሆኖም በሕይወቷ ቆርጣ ንጉሱ ዘንድ ገባች። ንጉሱንና ክፉውን ሀማን ግብዣ አዘጋጅታ ወደ ግብዣው እንዲመጡ ጠየቀቻቸው። በግብዣው ላይም ሀማ አይሁዳውያንን ለማጥፋት ያሴረውን ሴራ በመግለጥ ሀማን በንጉስ ፊት ከሰሰችው። ስለዚህም ሀማ መርዶክዮስን ለመስቀል ባዘጋጀው ላይ ራሱ ተሰቀለበት። መርዶክዮስ ግን ከፍ ከፍ አለ።

* ከዚያን ጊዜ ጀምሮም አይሁዳውያን ፑሪም የተባለውን በዓል በማክበር አስቴርን ያስቧታል።

ይህንን ጣፋጭ ታሪክ ማንበብ ከፈለጋችሁ በብሉይ ኪዳን በመፅሐፈ አስቴር ከምዕራፍ 1 – 10 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ታገኙታላችሁ።